# <u>የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)</u>

መግቢያ፡

የኢትዮጵያ ህዝብ ያለፉትን ሁለት አምባገነንና ጨቋኝ መንግሥታትን በከፍተኛ መስዋእትነት ታግሎ ቢያስወግድም፣ የስልጣኑ ባለቤት ለመሆንና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓትም ለመመስረት አለመብቃቱን በመገንዘብ፤

አሁንም አገራችን መሰረታዊ የሰብዓዊ መብቶች የተገፈፉባት፣ ዜጎች በእኩል የማይታዩባት፣ በዘርና በጎሳ እንዲከፋፈሉ የተደረገባትና አንድነቷ አደጋ ላይ የተጣለበት፣ በአምባገነንና የአንድ ፓርቲ አገዛዝ ስርዓት የተንሰራፋባት መሆኗን በማጤን፣

በአገራችን ያለውን የአፈናና የአፈና አምባገነናዊ ስርዓት ለመለወጥና በህገ-መንግስታዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመተካት የተባበረ ትግል እንደሚያስፈልግ በማመን፤

- በኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነትና የሕዝቡ የሥልጣን ባለቤትነትና ሉዑላዊነት ጽኑ ዕምነት ያላቸው፣
- ሁሉም የሀገሪቱ ዜጎች በህግ ፊት እኩል መሆናቸዉን የተቀበሉ፣
- ፍትኅ የሰፈነበትና የህግ የበላይነት የተረጋገጠበት ሥርዓት አስፈላጊነት የሚያምኑ፣
- በድርጅቶች ውስጥና መሃከል ዴሞክራሲያዊነትን መመሪያ ያደረጉና በሥራ የሚያውሉ፣
- በስልጣን ላይ የሚገኘው የህወሓት/ኢህአደግ አገዛዝ ለዴሞክራሲ መስፈንና ለብልጽግና እንቅፋት የሆነ ስርዓት በመሆኑ መወገድ እንዳለበት የተቀበሉ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪል ማህበራትና በርካታ አገር ወዳድ ግለሰቦች ከግንቦት 10 እስከ ግንቦት 13 ፣ 2004 ዓ.ም በካናዳ ያደረጉት ጉባኤ በጋራ ለመታገል ወስነዋል።

## <u>ዓላማና ተግባራት</u>

1 በቀጣይ ውይይትና ድርድር ሁሉም ኢትዮጵያዊ የዴሞክራሲና የአንድነት ሀይሎች በአንድነት እንዲመጡና ትግላቸውን እንዲያስተባብሩ ማድረግ። የተቃዋሚውን አቅም መገንባት።

2 በተባበረ ሕዝባዊ ትግል አምባገነኑን አገዛዝ ከስልጣን ማስወገድ።

3 በአገር ቤትና ውጭ ያሉ ሁሉም የፖለቲካና ሲቪክ ማህበራት፣ ለዴሞክራሲ በሚደረገው ትግል ጉልህ አስተዋጽዖ ያደረጉ ታዋቂ ግለሰቦችና የማህበረሰብ መሪዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት ተቋማት ተወካዮች በሚሳተፉበት ብሄራዊ ጉባኤ ከ2 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ብቻ የሚቆይ የሽግግር መንግሥት መመስረት

4 የኢትዮጵያ ህዝብ የስልጣን ምንጭና ባለቤትነቱን የሚያረጋግጥባት፤ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩባት፤ዜጎች በእኩልነት፤ በመፈቃቀድና በመተሳሰብ አብረዉ የሚኖሩባት፤ሀገራዊ አንድነቷ የተረጋገጠባት፤ የብሄሮች ባህልና ቋንቋዎች የሚከበሩባትና የሚበለጽጉባት፤ የእምነት ነጻነት የሚከበርባት፣ የመድበለ ፓርቲ የፖለቲካ ሥርዓትና ተሳትፎ የሚረጋገጥባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመመስረት መሰረት መጣል።

5.የአገሪቱ ዜጎች በሞላ፤ ምንም አይነት በብሄረሰብ፤ በቋንቋ፤ በሃይማኖት፤ በጾታ ወዘተ. ልዩነት ላይ የተመሠረተ አድልዎ ሳይደረግባቸው በሰላም የመኖር፤ በፈቀዱት ቦታ የመኖርና የመዘዋወር፤ ቤተሰብ የመመስረትና ንብረት የማፍራት፤ የመስራት፤ የፈቀዱት የፖለቲካ ወይም ሌላ ድርጅት አባል የመሆንና ያለመሆን፤ ገደብ የሌለዉ መብታቸውን ማስከበር

6.የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች ሳይሸራረፉ ተግባራዊ እንዲሆኑና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ ማድረግ

7.በሽግግሩ ወቅት የኅብረተሰቡ ማህበረሰባዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወት ያለምንም መናጋት፤ ፀጥታው ተከብሮለትና ሠላም ተረጋግቶለት፤ ሁሉም በተሰማራበት የምርትና የግልጋሎት ሥራ መስክና ስምሪት ላይ በህግና ሥርዓት እንዲቀጥል ማድረግ።

8.የኢትዮጵያን የግዛት አንድነትና የህዝቡን ልዕልና ባልተጻረረ መልክ ብሄረሰቦች የውስጥ አስተዳደራቸውን የመምራት ቋንቋዋቸውን የመጠቀምና የማዳበር፤ባህላቸውን እሴቶቻቸውንና ታሪካዊ ቅርሶቻቸዉን የመንከባከብ መብቶቻቸውን ማስከበር

9. ለአገሪቱ ህገ-መንግሥት ብቻ ታማኝና ተጠሪ የሆነ ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ቁጥጥርና ተጽእኖ ውጭ የሆነ ብሄራዊ የአገር መከላከያ ሠራዊት የሚፈጠርበትን ዕቅድና ቅድመ ዝግጅት ማድረግ

10. ህገ-መንግስቱን የሚመረምርና የአስፈላጊ የሆኑ መሻሻሎችን የሚያደርግ ከሁሉም ህብረተሰብና የፖለቲካ ኃይሎች ተዋጽዖ ያለው የህገ-መንግስት አርቃቂ ኮሚሽን ማቋቋም። የሚያቀርበውን ረቂቅም በህዝበ ውሳኔ ማጸደቅ።

11. ለህገመንግሥታዊ ሥርዓት ምስረታና ለቋሚ መንግስት ምርጫ የሚረዱ የህዝብን አመኔታ ያገኙ ተቋማትን መመስረት።

12. በነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ለሚመረጥ መንግሥት ሥልጣኑን ማስረከብ

## አበይት ተግባራት

1 ከላይ በተጠቀሱት፤ በተለይም በ ተ.ቁ. 3.1 የተዘረዘሩትን የጋራ አላማዎች የሚቀበሉ ድርጅቶችን፤ የፖለቲካ፤ የሲቪክ፤ የሙያና ወዘተ ማህበራትንና ግለሰቦችን ኅብረቱን እንዲቀላቀሉ የማያቋርጥ ጥረት ማድረግ

2. ህብረቱ ትግሉን ለማራመድ የሚያስፈልጉትን ገንዘብና ቁሳቁሶች፤ በራስ በመተማመን የኢኮኖሚ አቅም ለበማጎልበት የሁሉም ዜጋ ተሳትፎ ለማግኘት መጣር

3. የኅብረት ትግሉ አድማስ የሚሰፋበትን፤ የውጭና የውስጡ የሚተሳሰሩበትን አጠቃላይ አቅጣጫ ያሳያል፤ ለተግባራዊነታቸው ይሠራል

4. ከልዩ ልዩ መንግስታትና አለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት መፍጠር፤ በኢትዮጵያ ለሰላምና ለዴሞክራሲ መስፈን ለሚደረገዉ ትግል የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ድጋፍና ለማግኘት መሥራት